# ዜና መጽሔት

በኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሐዊ ዜና መጽሔት ኅዳር ፳፻፯ ዓ.ም.

## ዘጠነኛው የብሔር፣ብሔረሰቦች ቀን በድምቀት ተከበረ

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሠራተኞች፣ ዘጠነኛውን የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን እና የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት የጸደቀበትን ሃያኛውን ዓመት በዓል በኢንስቲትዩቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ኅዳር 26 ቀን 2007 ከቀኑ ስምንት ሰዓት ጀምሮ በተለያዩ ዝግጅቶች አከበሩ፡፡

አቶ ወንዱ ለገሰ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር፣ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ቀኑን ማክበር ያስፈለገው የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በትግላቸው የተጎናጸፏቸውን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ተጠቅመው በእኩልነት ላይ በተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት እየገሰገሱ መሆናቸውን የሚያስገነዝቡበት ዕለት በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ደበሌ ለማ፣ የኢንስቲትዩቱ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ቡድን አስተባባሪ “ህገ መንግሥት፣ ብዝሃነት፣ ልማት፣ ዴሞክራሲና ብሔራዊ መግባባት” በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበው ሠፊ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡





ወደ ገፅ 6 የዞረ

## በመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ላይ ስልጠና ተሰጠ

በወሳኝ የአገሪቱ ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባትን በመፍጠር፣ ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ በመላቀቅ የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ተግባር ልዕልናን ለማረጋገጥ ተግተው እንደሚሰሩ የሦስቱ ተቋማት መካከለኛ አመራሮችና ፈጻሚዎች አስታወቁ፡

ይህን ያስታወቁት፤ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መካከለኛ አመራሮችና ፈጻሚዎች ከጥቅምት ፲፩ ቀን እስከ ኅዳር 05 ቀን 2007 ዓ.ም በመንግስት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ላይ ሲሰጥ የነበረው ስልጠና ሲጠናቀቅ ባወጡት የአቋም መግለጫ ነው፡፡

ስልጠናው የተካሔደው በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሲሆን ከሦስቱ ኢንስቲትዩቶች የተወጣጡ 550 ሠራተኞች በሁለት ዙር ተከፍለው ለ፲ ቀናት ሰልጥነዋል፡ ለሰልጣኞቹ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግልና አገራዊ ኅዳሴያችን፣ የተሐድሶ መስመርና የኢትዮጵያ ኅዳሴ፣ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ትግላችን እና ፈተናዎቹ፣ የኢፌዲሪ ሕገመንግስትና ሴኩላሪዝም እና ልማታዊ ሲቪል ሰርቪስ የመገንባት ፋይዳና የሲቪል ሰርቪስ ሚና በሚሉ ርዕሶች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ስልጠናውን የሰጡት ከኢንዱስትሪ ሚንስቴር የተውጣጡ ሚንስትር ዴኤታዎች እና ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ኢንስቲትዩቶች ከፍተኛ አመራሮች ሲሆኑ

ወደ ገፅ 3 የዞረ

# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
# ዜና መጽሔት


በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዜና መጽሔት

ኅዳር ፳፻፯ ፤ ቅጽ 1 ቁጥር 1

ዋና አዘጋጅ

ብርሃኑ ስርጃቦ

አዘጋጆች

ዕዝራ ኃይለማርያም
ደበሌ ለማ
ሲሳይ አስታጥቄ
ሰብስቤ ባዩ

የገጽ ንድፍና ቅንብር

ጸደይ ተፈሪ

ፎቶ ግራፍ

መቅደስ መንግስቴ

አድራሻ

ስልክ ቁጥር 251 – 11- 4391700
251 – 11- 4391682
ፋክስ 251 – 11- 4392259
ፖ.ሳ.ቁ 24692 Code 1000

ድረ ገጽ www.elidi.org contact@elidi.org


በዚህ እትም

-የአዘጋጁ መልዕክት
-ዜናዎች
-የወሩ ምርጥ ጥቅስ
-የወሩ ምርጥ ካርቱን/ ፎቶ




## የዋና አዘጋጁ መልዕክት

የዘንድሮው ኅዳር በርካታ አገራዊ ጉዳዮች እና ሁነቶች የተከናወኑበት ወር ነው ። ዘጠነኛው የብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀንና የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት የጸደቀበት ሃያኛው ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሯል፡፡
በዓሉ የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሕገመንግስታቸው አማካይነት የፈጠሩት በእኩልነት፣ በወንድማማችነት ላይ የተመሰረተ አንድነትና ጥንካሬያቸውን ለመላው ዓለም ያሣዩበት እለት ነው፡፡ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሰራተኞችም ይህን በዓል በተለያዩ ዝግጅቶች አክብረዋል።

በወሳኝ የአገሪቱ ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባትን በመፍጠር፣ ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ በመላቀቅ የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ተግባር ልዕልናን ለማረጋገጥ ተግተው እንደሚሰሩ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መካከለኛ አመራሮችና ፈጻሚዎች አስታውቀዋል፡፡ ይህን ያስታወቁት ከጥቅምት 11 ቀን እስከ ኅዳር 05 ቀን 2007 ዓ.ም በመንግስት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ላይ በሁለት ዙር ሲሰጥ የነበረው ስልጠና ሲጠናቀቅ ባወጡት የአቋም መግለጫ ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ በወሩ ውስጥ ካከናወናቸው አቢይ ስራዎች ውስጥ በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው የቆዳና ቆዳ ውጤቶችን በማምረት ላይ በተሰማሩ አካላት ዘንድ የሚስተዋሉ ችግሮችን በማስቀረት አምራቾቹን ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርግ በክላስተር ተደራጅተው ለመስራት የሚያስችል ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት በዩኒዶ ተዘጋጅቶ ለባለድርሻ አካላት ለውይይት ያቀረበው በዚሁ ወር ነው፡፡

የዩኒዶ ከፍተኛ ኤክስፐርቶች ያጠኑት የጋራ ፍሳሽ ማጣሪያ ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት የቆዳ ፋብሪካዎች የጋራ ፍሳሽ ማጣሪያ በባለድርሻ አካላት ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ኢንስቲትዩት ከሕንድ የማዕከላዊ የቆዳ ምርምር ኢንስቲትዩት (CLRI) እና ከጫማ ዲዛይን ልማት ኢንስቲትዩት (FDDI) ጋር በተደረገዉ የቁርኝት ፕሮጀክት አጋርነት ስምምነት መሠረት ያዘጋጃቸውን የማስተማሪያ ማኑዋሎች ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ቢሮ አስረክቧል፡፡
ኢንስቲትዩቱ በርካታ ቁም ነገሮችን ያከናወነበት ወር ቢሆንም ባለው የቦታ ውስንነት የተነሳ የተወሰኑትን ብቻ ለማቅረብ ሞክረናል፡፡ በዚህ በቆኢልኢ (ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት) ዜና መጽሔት ፤ከዜና በተጨማሪ ጥቅሶችና ካርቱን ስዕሎች(ፎቶ) ተካተዋል፡፡
ቆኢልኢ ዜና መጽሔት ተነባቢ የሚሆነው፣ የኢንስቲትዩቱ ባልደረቦች እና በለድርሻ አካላት መረጃዎችን በመስጠት ተሳትፎ ሲያደርጉ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ከዚህም አንጻር ለዜና መጽሔቱ የሚሆኑ መረጃዎችን በማቅረብ ተሳትፎ ታደርጉ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ ☐



# በመንግስት ፖሊሲና . . .

ዴሞክራሲያዊ መንግስት የተቀየሱትን የዕድገት አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎቹንና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ይጠቅማል ብለዋል፡፡

አቶ አባተ አርጋው የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር



ሰልጣኞቹም በሁለቱም ዙር በ12 ቡድኖች ተከፍለው በተሰጡት ትምህርቶች ላይ ውይይት አካሂደዋል፡፡

በተደረገው የቡድን ውይይት ላይ ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጉዳዮች በኃይል መድረክ ቀርበው በአሰልጣኞቹ በቂ ገለጻ ተሰጥቷል፡ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ረዳት ተመራማሪ ወይዘሮ መንበረ ክንፈ በሰጡት አስተያየት ስልጠናው በልማታዊና

እንደተናገሩት፣ ስልጠናው በፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም የኢፌዴሪ ሕገመንግስትና ሴኩላሪዝም እና ልማታዊ ሲቪል ሰርቪስ የመገንባት ፋይዳና የሲቪል ሰርቪስ ሚናን በተመለከተ የተሻለ ዕውቀትና ግንዛቤ ማግኘት እንደቻሉ ገልጸዋል፡፡ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሆኑት ወይዘሮ

ፍሬሕይወት ኪዳኔ በበኩላቸው እንዳሉት ለአስራ አንድ ቀናት የወሰዱት ስልጠና መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞችን እንዲያውቁ አግዟቸዋል፡፡

በቡድን የተደረጉ ውይይቶች ግልጽና ዲሞክራሲያዊ መሆኑ፣ ግንዛቤያቸውን ከማስፋቱም በላይ የአገሪቱን ኅዳሴ ቀጣይነት ለማረጋገጥ፣ በተሰማሩበት ስራ መስክ ውጤታማ ተግባራትን ለማከናወን በትጋት እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

በሁለቱም ዙሮች ስልጠና ማጠቃለያ ላይ፣ ሰልጣኞቹ በስልጠናው ላይ በነበራቸው ተሳትፎ መጠን መሰረት አድርጎ በተካሔደው ግምገማ ደረጃ ተሰጥቷቸዋል፡

ስልጠናውን ምክንያት በማድረግም የሦስቱ ተቋማት መካከለኛ አመራሮችና ፈጻሚዎች የተሐድሶ ፕሮግራም ህዳር 09 ቀን በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተካሂዷል፡፡በዚሁ ፕሮግራም ላይ ሰልጣኞቹ ያወጡት ባለዘጠኝ ነጥብ የአቋም መግለጫ የቀረበ ሲሆን በስልጠናው ወቅት ሰልጣኞች በኢንስቲትዩቱ ክበብ የተሟላ መስተንግዶ እንዲያገኙ እና አዳራሽና የቡድን መወያያ ክፍሎችን በማመቻቸት የጎላ አስተዋጽኦ ላበረከተው የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ከኢንዱስትሪ ሚንስቴር የተበረከተለትን ምስክር ወረቀት ተቀብሏል፡፡



አቶ አባተ አርጋው



ወ/ሮ መንበረ ክንፈ



ወ/ሮ ፍሬህይወት ኪዳኔ

# ስለ ጉንዳኖች በጥቂቱ

በአንድ የጉንዳን ስብስብ ውስጥ ሶስት ዓይነት ጉንዳኖች አሉ፡፡ ሰራተኛ፣ ንግስት እና አውራ ጉንዳን በመባል ይታወቃሉ፡፡ እያንዳንዱ የጉንዳን አይነት የየራሱ ተግባሮች አሉት፡፡ በውስጣቸው ያለውን አደረጃጀት መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል ያላቸው ከመሆኑም በላይ፣ በአንድ የጉንዳን ስብስብ ውስጥ መሰራት ካለበት ነገር ምንም ሳይሰራ አይቀርም፡፡ ከዚህ የጉንዳን ተግባር፣ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እንደአቅሙ የራሱን ድርሻ በመውሰድ መስራት እንዳለበት፣ ራውንም ለነገ ማለት እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ምንጭ፡ www.miraclesinants.com

# ኢንስቲትዩቱ አምራቾቹን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ እየሠራ ነው



በኢትዮጵያ ውስጥ በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዝ ተደራጅተው የቆዳና የቆዳ ውጤቶችን በማምረት ላይ በተሰማሩ አካላት ዘንድ የሚስተዋሉ ችግሮችን በማስቀረት አምራቾቹን ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርግ ጥናት ማዘጋጀቱን የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ከተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (ዩኒዶ ) ጋር በመተባበር በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዝ ተደራጅተው በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ «የኢትዮጵያን የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር» በሚል መርህ በአዲስ አበባ ከተማ በሦስት ክፍለ ከተሞች በሚገኙ የቆዳ ውጤቶች አምራቾችና ሻጮች ላይ ያካሄደውን የክላስተር ልማት የጥናት ውጤት ህዳር 17 2007 ዓ.ም ይፋ አድርጓል።

ጥናቱ ይፋ በሆነበት ወቅት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሰ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዝ ተደራጅተው በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካላት ትኩረት በመስጠት ይበልጥ ውጤታማ ማድረግና የአምራቾቹን አቅም ማጎልብት ያስፈልጋል።

እንደ አቶ ወንዱ ገለጻ፤ በሦስት ክፍለ ከተሞች የተካሄደው የክላስተር ልማት ጥናት ዘርፉን ለማሳደግና በዘረፉ የተሰማሩ የተለያዩ አካላትን አቅም በማጎልበት የምርታቸውን ጥራት ለማሻሻልና በዓለም አቀፍና በአገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ የጎላ ጠቀሜታ አለው።

ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት የእርስ በእርስ የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበትንና የግብዓት አቅርቦት በቀላሉ የሚያገኙበትን መንገድ የማመቻቸት ሥራ እየሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ወንዱ፤ በቀጣይ ወደ ዘርፉ የሚገቡ አዳዲስ አምራቾችን ለመፍጠርና ቀደም ሲል የነበሩትን ይበልጥ ለማጠናከር ሁሉም በጋራና በቅንጅት መሥራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በዕለቱ በአዲስ አበባ በሦስት ክፍለ ከተሞች በተለይም በመርካቶ፤ በቂርቆስና በጉለሌ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ አምራቾች ላይ የተካሄደውን የክላስተር ልማት የጥናት ውጤት ያቀረቡት የዩኒዶ የክላስተር ልማት ስፔሻሊስት አቶ አሊጂራ ኩማ ፤ጥናቱ ለዘጠኝ ወራት ያህል ሲካሄድ መቆየቱን ጠቁመዋል። በጥናቱ መሠረት በአሁኑ ወቅት አምራቾቹ ከእዚህ ቀደም ባልተለመደ መልኩ የምርታቸውን ሦስት በመቶ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ቢችሉም እያመረቱ ያሉት ግን ማምረት ከሚችሉበት አቅም ሃያ በመቶ ብቻ መሆኑን አመልክተዋል። ይህም አሁን ለዘርፉና ለእምራቾቹ ውጤታማነት ይበልጥ መሥራትን እንደሚጠይቅ ለማወቅ መቻሉን ገልጸዋል።

አምራቾቹ አሁን ባሉበት ደረጃ ሙሉ አቅማቸውን ቢጠቀሙ በዓመት ሦስት መቶ ሺ ደርዘን ጫማ ማምረት እንደሚችሉ ያመለከቱት አቶ አሊጂራ፤ በቴክኖሎጂና በገንዘብ ቢደገፉ ደግሞ ከእዚህ በላይ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ አመልክተዋል።

አቶ አሊጂራ እንደገለጹት፤ በቆዳ ውጤቶች ላይ የተሰማሩ አምራቾች ብቻቸውን በሚሠሩብት ወቅት ውጤታማ መሆን ይሳናቸዋል። በመሆኑም የክላስተር ጥናቱ በተደራጀ አቅምና በቴክኖሎጂ፤ በእውቀትና ዘመናዊ አሠራርን በተከተለ መልኩ በመደራጀት ውጤታማ ለመሆን የሚያስችላቸው ነው። በመንግሥት በኩልም አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግላቸው ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር አብራርተዋል።

በጥናቱ መሠረት ጥቃቅንና አንስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ የማደራጀቱን ሥራ በበላይነት የሚመራው ሲሆን፤ የቆዳ ልማት ኢንስቲትዩት የተደራጁትን አካላት አቅም የማጎልበት፤ የገበያ ትስስሮችንና የግብዓት አቅርቦትን በቀላሉ የሚያገኙበትን መንገድ የማመቻቸት ሥራ ይሠራል።

# በጥናት ላይ ውይይት ተደረገ

በሞጆ ቆዳ ኢንዱስትሪ ዞን የሚገኙ የቆዳ ፋብሪካዎች የሚያስወግዱትን ቆሻሻ፣ በጋራ ፍሳሽ በማከም የአካባቢ ክብካቤን ለማስጠበቅ በተሰራው ጥናት ላይ ውይይት ተደረገ፡፡

በናዝሬት ከተማ ኅዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም በድሬ ኢንተርናሽናል ሆቴል በተደረገው ውይይት ላይ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች፣ የቆዳ ፋብሪካ አመራሮች እና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል፡፡

ክቡር አቶ ታደሰ ኃይሌ የኢንዱስትሪ ሚንስትር ዴኤታ እንዳስታወቁት መንግስት የቆዳ ኢንዱስትሪን ለማሳደግ ቅድሚያ ትኩረት ከሰጣቸው ዘርፎች አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በሞጆ ቆዳ ኢንዱስትሪ ዞን የተጠናውን የዝርዝር አዋጭነት ጥናት ተግባራዊ ለማድረግ ፣ የአካባቢ ክብካቤን በዘላቂነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ልማት እና በኢንቨስትመንት

ድጋፍ አሰጣጥ ላይ የአገር ውስጥና የውጭ ኤክስፐርቶች ተካፋይ ሆነዋል ::

በተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (ዩኒዶ)፣የአግሮ ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ዩኒት ኃላፊ አውሮሊያ ካላብሮ በበኩላቸው እንዳሉት በሞጆ ቆዳ ኢንዱስትሪ ዞን የተጠናውን ጥናት ውጤታማ መሆን ለምስራቅ አፍሪካ አገሮች አርአያ ሊሆን ይችላል፡፡

በጥናቱ እንደተመለከተው ከሆነ ፣ የቆዳ ፋብሪካዎች ወደ ወንዝ የሚለቀቁት ያልታከመ ቆሻሻ ወንዙን በሚጠቀሙ አካላት ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡

በዚህም የተነሳ ያልታከመና አገልግሎት ላይ የሚውል የተበከለ ውሃ በውሃ ላይ የሚደረገውን አለአስፈላጊ አጠቃቀም እና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ነው፡፡

በሞጆ ቆዳ ኢንዱስትሪ ዞን የተጠናው ጥናትም ቆዳ ፋብሪካዎች ትስስር በመፍጠር ተፈጥሮን በመንከባከብ ማምረት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል፡፡

በሞጆ የሚገኙ ቆዳ ፋብሪካዎች ቆሻሻ ማከሚያ የሚገነባው በሁለት ምዕራፎች ሲሆን የመጀመሪያውን ምዕራፍ ለመገንባት 58 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡

# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተለያዩ የማስተማሪያ ማኑዋሎችን ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ቢሮ አስረከበ

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከሕንድ የማዕከላዊ የቆዳ ምርምር ኢንስቲትዩት (CLRI) እና ከጫማ ዲዛይን ልማት ኢንስቲትዩት (FDDI) ጋር በተደረገዉ የቁርኙት ፕሮጀክት አጋርነት ያዘጋጃቸውን የማስተማሪያ ማኑዋሎች ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ቢሮ አስረክቧል፡፡

ማኑዋሎቹን በማስረከብ መርሐ ግብር ላይ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሰ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለውጥ ለማምጣት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለመምራት እና ለማከናወን የተቋቋመ ነው፡፡

በዘርፉ የሚሰማራው የሰው ኃይል ደግሞ በዋነኛነት የሚፈራው በቴክኒክ እና ሞያ ተቋማት በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ የመማሪያ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና የአሰልጣኞች ሰለጠና በመስጠት ለቴክኒክ እና ሞያ ተቋማቱ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል ዋናዳይሬክተሩ፡፡ይህም በተቋማዊ አቅም ወጥ የሆነ ሀገራዊ አቅም መገንባት እንደሚያስችል ገልፀዋል፡፡

የኢንስቲትዩቱ የትምህርት እና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ፀጋዬ ተፈራ በበኩላቸው በዘርፉ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ለማፍራት ከክልሎች ጋር በተሰራዉ ስራ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልልን ጨምሮ በአምስት ክልሎች የሰው ኃይል የማልማት ስራ መከናወኑን አስታዉቀዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከክልሎቹ ለተወጣጡ ባለሙያዎች በሶስት ዙር የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠቱንም ጠቁመዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የሙያ ደረጃዎች መለየቱን፣ ስርዓተ ትምህርት ተቀርፆም በፌደራል የቴክኒክና ሞያ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲ በኩል ለሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲደርስ መደረጉን አመልክተዋል፡፡ በጫማ አመራረት፣በቆዳ አልባሳት እና በቆዳ እቃዎች አመራረት የመምህሩ መመሪያ፣የተማሪዉ መመሪያ እና የምዘና ሂደትን የሚያሳዩ ማኑዋሎች መዘጋጀታቸዉንም ዳይሬክተሩ አስታዉቀዋል፡፡

የክልሉ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አጥናፉ አስፋዉ በበኩላቸዉ ጥራት ያለው ሰልጣኝ ለማፍራት ጥራት ያላቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች መኖር ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዉ ኢንስቲትዩቱ በዚህ ረገድ እየሰጠ ያለዉን ድጋፍ አድንቀዋል፡፡

በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ የክልሉ




ቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት የልቀት ማዕከል እንዲሆኑ ከኢንስቲትዩቱ ጋር በመተባበር እንደሚሰራም አስታውቀዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ሀላፊነቱን ወስዶ በዘርፉ ጥራት ያለው ስልጠና እንዲሰጥ በመስራቱም አመስግነዋል፡፡ ኢንስቲትዩቱ ለአሰልጣኞች በሰጠዉ የስልጠና እድል ከክልሉ 9 የቴክኖሎጂ ሽግግር 6 ደግሞ የቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ባለሞያዎች ስልጠና ማግኘታቸዉም ተጠቁሟል፡፡

ማኑዋሎቹ አሰልጣኙ እና ሰልጣኙ ጋር ደርሰው ስልጠናው በማኑዋሉ መሰረት ሲሰጥ ብቻ የስልጠናዉን ጥራት ማረጋገጥ እንደሚቻል የተናገሩት ዳይሬክተሩ ቢሮዉ ይህን በአግባቡ በማድረሱ ረገድ ሀላፊነቱን እንዲወጣ ጠይቀዋል፡፡

በክልሉ በአሁኑ ወቅት 147 ሰልጣኞች በዘርፉ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመዉሰድ ላይ እንደሚገኙ እና በሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በደረጃ አንድ እና ሁለት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማሰልጠን መጀመሩንም አስታዉቀዋል፡፡ በኮሌጁ ደረጃዉን የጠበቀ ወርክሾፕ ለማስገንባትም እንቅስቃሴ መጀመሩ ተመልክቷል፡፡

የማስተማሪያ ማንዋሎቹን የቆዳኢንዱትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሰ ለደቡብ ቴክኒክ እና ሞያ ትምህርት እና ሰልጠና ቢሮ ምክትል ሀላፊ ያስረከቡ ሲሆን በማኑዋሉ አጠቃቀም ዙሪያ በሁለቱ ተቋማት የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሟል፡፡

## ዘጠነኛው የብሔር ፣ . . .

በዓሉን በተመለከተ በኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት “በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ለምን ይከበራል?” በሚል ርዕስ ብሮሸር ተዘጋጅቶ ለሠራተኞች የተሰራጨ ሲሆን በዓሉን የተመለከቱ መልዕክቶች በባነር እና በወረቀቶች ተዘጋጅተው በአዳራሽ ውስጥና በማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ ተለጥፈዋል፡፡





## ማረፊያ

አንድ ባለጠጋ አንድ ዳውላ እህለ ከቤቱ ተሰረቀበትና ወደ ዳኛ ሔዶ ነገሩን ሁሉ ነገረ፡፡ ዳኛውም የቤትህን ሰዎች ሁሉንም ሰብሰብህ አምጣልኝ አለው፡፡እርሱም ሰብስቦ አቀረበ፡፡ ዳኛውም ብዙ በትር አምጥቶ ሁሉንም በትክክል አስቆረጠው፡፡ ከዚያም በኋላ ለዚያ ሰው ቤተሰዎች ለሁሉም አንዳንድ በትር ሰጣቸው፡፡ሲሰጣቸውም ነገ በዚህን ጊዜ ተመልሳችሁ ኑ፤ ነገር ግን የጌታውን እህል የሰረቀ ሰው በትሩ አንድ ጋት በልጦ ያድራል እያለ ሰጣቸው፡፡ ያ የጌታውን እህል የሰረቀ ሰው ይህን በሰማ ጊዜ ማታ ከበትሩ አንድ ጋት ቆረጠለት፡፡ በማግስቱ በዚያው በታዘዙበት ሰዓት ሁሉም ተሰብስበው ወደዳኛው ቤት ሔዱ፡፡ ዳኛውም ሁላችሁም የሰጠኋችሁን በትር አምጡ ብሎ በአንድነት ቢያቆመው የሌባው በትር አጥሮ ተገኘ፡፡ ከዚህ በኋላ እጁ ተይዞ ቢመረመር መሰረቁን አምኖ ቅጣት ተፈረደበት፡፡

ኀሩይ ወልደስላሴ ሱካርና ወተት 16ኛ ተረት ከተባለው መጽሐፍ የተወሰደ






# ካይዘን ለቆዳ ኢንዱስትሪ  እድገት ጉልህ ድርሻ ያበረክታል

ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ለሚገኘው የቆዳ ኢንዱስትሪ፣ ካይዘን ጉልህ ሚና እንዳለው ሰልጣኞች አስታወቁ፡፡
ሰልጣኞቹ ይህን የተናገሩት፣ቀደም ሲል ለኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች የተሠጠውን የካይዘን ስልጠና ላልሰለጠኑ ባለሙያዎች ከኅዳር 22 – 24 /07 የተሰጠውን ስልጠና በተሳተፉበት ወቅት ነው፡፡

ስልጠናው የተሰጠው በኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች ሲሆን ከቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡

አቶ ደፋሩ አንተነህ በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከፍተኛ የአሰራር ማሻሻያ ባለሙያ ሲሆኑ በስልጠናው ከተሳተፉት አንዱ ናቸው፡፡
አቶ ደፋሩ እንደሚሉት ካይዘን ለመደበኛ ስራ ብቻ ሳይሆን ለግል ሕይወትም ይጠቅማል። ብክነትን በመቀነስና የሥራ ጥራትን በማምጣት የተመሰከረለት ፍልስፍና መሆኑን የገለጹት ባለሙያው ኢንስቲትዩቱ ከሐምሌ 2007 ዓ.ም ጀምሮ ሁለተኛውን ምዕራፍ የካይዘን ትግበራ መጀመር እንዲችል ጠንክሮ በመስራት ላይ መሆኑን አቶ ደፋሩ አንተነህ አስታወቀዋል፡፡ ከስልጠናው

ጠቃሚ ትምህርት ማግኘታቸውን ጨምረው ገልጸዋል፡፡
አቶ ደነቦ መኩሪያ በኢንስቲትዩቱ የቴክኒካል እና ሙያዊ ትምህርትና ስልጠና ቡድን አስተባባሪ እንደሚሉት ኢንስቲትዩቱ ካይዘንን በመተግበሩ ተጠቃሚ በመሆን ላይ መሆኑን ጠቁመው  ስልጠናው የአመለካከት ለውጥ እንዳመጣላቸው ገልጸዋል፡፡
የካይዘን ፍልስፍና  ቀጣይነት ያለው ለውጥ ማምጣት በመሆኑ፣ በየዕለቱ እድገት ያለው ለውጥ ለማምጣት በትጋት እንደሚሰሩ አመልክተዋል፡

ወይዘሪት መቅደስ መንግስቴ ፣የኢንስቲትዩቱ አውዶ ቪዥዋል ባለሙያ በበኩላቸው እንዳሉት ስልጠናው የአመለካከት ለውጥ በማምጣት በስራቸው ላይ የእኔነትና የይቻላል መንፈስ ያዳበረላቸው መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በስልጠናው ያገኙትን እውቀት በስራ በመተግበር ብክነት በመቀነስ፣ምርታማነትን በማሳደግና የምርታቸውን ጥራት በማሳደግ ውጤታማ እንደሚሆኑ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል፡፡
አቶ ደፋሩ አንተነህ እንደገለጹት በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት 47 የካይዘን ልማት ቡድኖች ያሉ ሲሆን፣



አቶ ደፋሩ አንተነህ



አቶ ደነቦ መኩሪያ

ካይዘንን በመተግበር የሚያበረታታ ውጤት አግኝቷል፡፡ የካይዘን ሞዴል በመሆን ለቆዳ ፋብሪካዎች ካይዘንን ማሸጋገር አለበት ብለዋል፡፡

## ከከበደ ሚካኤል ግጥሞች የተወሰደ

ሕይወት ጦርነት ነው ዋጋህን የሚያሣይ
መታገል ግድ ነው ስትኖር በዓለም ላይ ፡፡
በገዛ እጁ ወድቆ በቁሙ እየሞተ
መታገል ያልቻለ ልቡ እየታከተ
የሚያነሳው የለም በፍቅር በእርዳታ
በዚች በመሬት ላይ ፍጡር ካልበረታ
ጥንቱን አልተሰራም ለሰነፎች ቦታ፡፡

## አባባሎች

- ብዙ ሰዎች ምክር ይቀበላሉ፣ ጥቂቶች ብቻ ያተርፉበታል  (አርስቶትል)
- ሰው ሊሞትለት የሚችለውን  ነገር ፈልጎ እስካላገኘ ድረስ ለመኖር ብቁ አይደለም (ማርቲን ሉተር ኪንግ)
- ራሳቸውን የሚረዱትን እግዚአብሔር ይረዳቸዋል ( ዳግማዊ ምኒሊክ)
- የተራበ  ሆድ ጆሮ የለውም (ዳግማዊ ምኒሊክ)
- በሁሉም ነገር አንድ ሰው መጨረሻውን ማሰብ አለበት (ዳግማዊ ምኒሊክ)
- በሁሉ ሰው ምክር ቤት የሚሰራ ሰው አስቀኝ ቤት ይሰራል (ዶ/ር ጆንሰን)